## ሙስናን ለመከላከል የማህበረሰቡ ሚና

በማህበረሰባችን ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል የሚለው አሉታዊ አባባል የተለመደ ነው፡፡ ይህ አባባል ሙሰኞች በድርጊታቸው እንዲበረታቱ በአንጻሩ ሙሰኞችን ለማጋለጥ የሚሞክሩ ካሉ ምቀኛ የሚል የውግዘት ካባ እንዲላበሱ ያደርጋል፡፡ ሙሰኞችን የሚያበረታታ በአንጻሩ ንጹሀንን የሚኮንን አመለካከት ባለበት የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ማስቀጣት አይቻልም፡፡ ስለዚህም ህብረተሰቡ የሙስና አፀያፊነትን በአግባቡ በመገንዘብ በሚከተለው መልኩ ሚናውን ሊወጣ ይገባል፡፡

- ሙስና ሲፈፀም ለህጋዊ አካላት ጥቆማ መስጠት፤
- ጉቦ ወይም እጅ መንሻ ከመስጠት መቆጠብ፤
- የህዝብና የመንግስት ሀብት እንዳይመዘበር መከላከል፤
- ታማኝና መልካም ስነ ምግባር ያላቸዉን ዜጎች እንዲፈጠሩ መስራት፤
- በውሳኔ አሰጣጥ እና ህዝባዊ ውይይቶች መሳተፍ፤
- በቤተሰብ ወይም በማህበረሰብ ውስጥ ታማኝነትን፣ ሀላፊነት መወጣትና የሌብነት ፀያፍነትን በማስተማር መልካም እሴቶች በትዉልዱ እንዲጎለብቱ ማድረግ፤
- መልካም ስነ ምግባርን ከሚገነቡ ተቋማት ጋር መተባበር፤

## ስነ ምግባራዊ ግለሰቦች እና ከሙስና የፀዱ ተቋማት መስተጋብር

በሥነ-ምግባር የታነፁ ግለሰቦችን ከሙስና የፀዱ ተቋማት እርስ በርስ በመደጋገፍ ዑደት ይፈጥራሉ፡፡ ለሥነ-ምግባር ዋጋ የሚሰጡ ዜጎች ከተቋማት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ይጠይቃሉ፤ ጠንካራ ስርዓት ያላቸው ተቋማት ደግሞ ሥነ-ምግባርን ያበረታታሉ፣ መልካም ሥነ-ምግባር እንዲጎለብት ይደግፋሉ፡፡

ዜጎች የተቋማት የአሰራር ስርአት ፍትሃዊ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ በተቋማቱ ላይ እምነት ይጥላሉ፤ ታማኝ ተቋማት ደግሞ በኃላፊነትና በሥነ-ምግባር የታነፁ አመራርና ባለሙያዎች ሲመሩ ለተገልጋይ ምቹና ፍትሀዊ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ይህ መስተጋብር የመተማመን፣ የተጠያቂነትና መልካም አስተዳደር በመገንባት የተገልጋዩንም እርካታ ማሳደግ ይችላል፡፡

**በስነ ምግባር ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ**


አድራሻ
በአራዳ ክ/ከ ወረዳ 1 ቸርችል ጎዳና ትንሳኤ ህንፃ 4ተኛ ፎቅ

ጥቆማ ለመስጠት
የነፃ ስልክ መስመር
8887

Addis Ababa Ethics and Anti-Corruption -ፀረ ሙስና

Addis Ababa Ethics Media

aanticoruption@gmail.com


# ትውልድን በስነ ምግባር፤ ተቋምን በአሰራር!

## 22ኛው ዓለም ዓቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን




ህዳር 2018



## ሥነ-ምግባር ያለው ትውልድ፤
## ከሙስና የፀዳ የአሰራር ስርዓት ያለው ተቋም!

በሥነ-ምግባር እሴቶች ላይ የተመሰረተትውልድ እና ከሙስና የፀዳ ስርዓት ጋር ራሳቸዉን አላምደዉ የሚሰሩ ተቋማት የዘላቂ ልማት፣ የማህበራዊ እምነት እና የመልካም አስተዳደር መሰረት ይሆናሉ። በሥነ-ምግባር የታነፁ ዜጎች በታማኝነት፣ በተጠያቂነትና በፍትሃዊነት የሚሰሩ ሲሆን የሙስና ተጋላጭነታቸዉን በአሰራር የዘጉ ተቋማት ደግሞ ቅልጥፍናን፣ ፍትሃዊነትንና የህዝብ አመኔታን ያረጋግጣሉ።

## ስነ ምግባራዊ ትዉልድ

- ጠንካራ የሞራል እና የስነምግባር እሴቶችን ያከብራል፤
- በማህበረሰቡ ውስጥ አርአያ ይሆናል፤
- ቃል ኪዳኖችን ያከብራል እና ለድርጊቱ ሀላፊነት ይወስዳል፤
- ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን አምርሮ ይታገላል፤
- የአሰራር ግልፀኝነትን ያበረታታል፤
- በማህበረሰብ አገልግሎት ውስጥ በንቃት ይሳተፋል፤
- የዜግነት ግዴታዉን በአግባቡ ይወጣል፤
- የህብረተሰቡ አብሮነት የሚያጠናክሩ የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎቶች ላይ በንቃት ይሳተፋል፤
- ፍትህን ለማስፈን ህጎችን፣ መብትና ግዴታዎችን እንዲሁም ኃላፊነቶችን ተገንዝቦ በአግባቡ ይፈፅማል፤
- ብዝሃነትን ያከብራል ለባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ግለሰባዊ ልዩነቶች ዋጋ ይሰጣል፤

## ለሙስና ተጋላጭ ያልሆነ ተቋም

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ባህሪያት የተላበሰ ተቋም ለሙስና ያለውን ተጋላጭነት በመቀነስ ለዜጎች ፍትሀዊ አገልግሎቶች ይሰጣል።

- በግልፅ፣ በፍትሃዊነት እና በተጠያቂነት ይሰራል፤
- ሌብነትን ለመከላከል ግልጽ የሆኑ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችን እና መመሪዎችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- ሌብነትን ለመከላከል ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ስረዓቶችን ይዘረጋል፤
- አዎንታዊ የስራ ባህልን የሚያጠናክርበት የእዉቅናና ሽልማት ስርዓት ይኖረዋል፤
- ቀልጣፋ፣ ወቅታዊ ፣ፍትሃዊ እና ጥራት ያለዉ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርአት ይኖረዋል፤
- ሥነ ምግባራዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን ሲፈጠሩ የሚስተካክልበት የቅሬታና አቤቱታ ስርዓት ይኖረዋል፤
- ቀጣይነት ያለዉ ተከታታይ የድጋፍ፣ ክትትል፣ምዘና እና ግብረ መልስ ስርዓት ይኖረዋል፤

## የተቋም አመራሮች ሚና

**የግለሰባዊ ባህሪን እና ተቋማዊ ታማኝነትን ለመቅረጽ አመራር ወሳኝ ነው፤**

- መሪዎች በተቋማት ዉስጥ መልካም ስነ ምግባር እንዲጎለብት ይሰራሉ፤
- በፍትሃዊነት እና ግልጽነት ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎችን ያስተላልፋሉ፤
- በተቋማት ዉስጥ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ያደርጋሉ ፤
- የሌብነት አደጋዎችን ይቀንሳሉ፤
- የተቋማት የሙስና ተጋላጭነትን ይቀንሳሉ፤
- መልካም እሴቶችን ለትዉልድ በማስተላለፍ የስነ ምግባር ባህል ዘላቂነትን ያረጋግጣሉ፤
- በሁሉም ደረጃዎች ተጠያቂነትን ያሰፍናሉ፤
- ለፍትሃዊነት፣ ለእኩልነት እና ለፍትህ ይሟገታሉ፤ መብቶችና ግዴታዎችን ያስከብራሉ፤ እንዲሁም አካታች ፖሊሲዎችን ይከተላሉ፤

